# ጋዜጣዊ መግለጫ

አሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ
2014/25

ለተጨማሪ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
ድረ-ገጽ - http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ መንግሥት ፊስቱላን ከኢትዮጵያ ለማስወገድ እገዛ ያደርጋል

***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም.፤*** ወደ 200 የሚጠጉ ፖሊሲ አውጪዎች፣ ውሳኔ ሰጪ አካላት እና የፊስቱላ ሕክምና ባለሙያዎች “በ2020 ፊስቱላን በማስወገድ ሕይወትን እንቀይር” በሚል መሪ ቃል በተዘጋጀ አገር አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ የፌዴራሉ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በወሊድ ወቅት የሚያጋጥም የፊስቱላ ችግርን እ.ኤ.አ. በ2020 ለማስወገድ የሚያስችል የድርጊት መርሃ ግብር የማዘጀት ሥራን በበላይነት በመምራት ላይ ይገኛል፡፡ ኮንፈረንሱንም ያዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብሩን ለባለድርሻ አካላት ለማስተዋወቅ እንዲሁም በዝግጅቱ የራሳቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትንና ዕቅዱን ይበልጥ የሚያዳብሩበትን ዕድል ለማመቻቸት ነው፡፡

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክ እንደተናገሩት ኮንፈረንሱም ሆነ በወሊድ ወቅት የሚከሰት ፊስቱላን ለማስወገድ የድርጊት መርሃ ግብር መዘጋጀቱ በጣም ጠቃሚ ርምጃ ነው፤ ምክንያቱም የፊስቱላ ችግር ህክምና ካልተደረገለት በሚያስከትላቸው የጤና፣ ሥነልቦና፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች የተነሳ በሴቶች ሕይወት ላይ አስከፊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

ፊስቱላ በተለይ በኢትዮጵያ የተለመደ ችግር ነው፡፡ በዩ ኤስ ኤ አይ ዲ እና በአውስትራሊያ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የገንዘብ ድጋፍ በቅርቡ የተደረገ የፊስቱላ ሁኔታ ትንተና ጥናት በኢትዮጵያ በዓመት 3,500 ሴቶች በወሊድ ወቅት የሚከሰት ፊስቱላ ችግር ተጠቂ እንደሚሆኑ ያመለክታል፡፡ እንዲሁም ከ37,500 የማያንሱ ሴቶች ላለባቸው የፊስቱላ ችግር ሕክምና ሳያገኙ ከችግሩ ጋር አብረው ይኖራሉ፡፡ የአሜሪካ መንግሥት ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳት እና ከፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዲሁም ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር በወሊድ ወቅት የሚያጋጥም ፊስቱላ ችግር ያለባቸውን ሴቶች በመለየት እና ሕክምና ወደሚያገኙበት ባለሙያ በመላክ በኩል ለሚሰሩ ስራዎች ድጋፍ ያደርጋል፡፡

እ.ኤ.አ. ከ2007 ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በመተባበር ታማሚዎች ወደ ሐምሊን ፊስቱላ ሆስፒታል ለህክምና ከመላካቸው በፊት፤ እንደ ማማከር፣ መመገብ እና ኢንፌክሽንን የሚከላከል ህክምና መስጠትን በመሳሰሉ አስፈላጊ የቅድመ ቀዶ ጥገና ዝግጅቶች ላይ እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ለሐምሊን ሆስፒታሎች በሚያደርገው ድጋፍ በመቶዎች የሚቆጠሩ የፊስቱላ ቀዶ ጥገናዎችን ወጪ ሸፍኗል፡፡

የአሜሪካ መንግሥት የፊስቱላን ችግር በመለየት ረገድ ባካበተው ልምድ እና ባስመዘገበው ስኬት የተነሳ ለፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተጨማሪ ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን፤ ግንዛቤ በመፍጠር፣ የፊስቱላ ችግር ያለባቸውን በመለየት፣ ለሕክምና በመላክ እንዲሁም መልሶ ወደ ማህበረሰቡ በመቀላቀል በፓዝፋይንደር እና ጆን ስኖው ኢንኮርፖሬትድ አማካኝነት በሚሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ በሚተገበረውና ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ በሚመራው **የተቀናጀ የቤተሰብ ጤና መርሃ ግብር** በኩል ይከናወናል፡፡ አምባሳደር ሃስላክ “በአዲስ መልኩ በጋራ ለመስራት እና በዚህ አሰቃቂ ችግር የምትሰቃየውን እያንዳንዷን ኢትዮጵያዊት ሴት ለመለየት ለሚደረገው አዲስ ጥረት ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነን፡፡” በማለት ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በ2020 ፊስቱላን አስወግዶ የሴቶችን ሕይወት ለመቀየር በሚያደርገው ጥረት ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉ በመሆኑ፤ ኮንፈረንሱ ስኬታማ እንደሚሆን የአሜሪካ መንግሥት እምነት ነው፡፡

###